# የማቴዎስ ወንጌል/Matthew

## ምዕራፍ /Chapter 4

| | |
|---|---|
| 1 ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው ፥ | [1] Then was Jesus led up of the Spirit into the wilderness to be tempted of the devil. |
| 2 አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ። | [2] And when He had fasted forty days and forty nights, he was afterward an hungred. |
| 3 ፈታኝም ቀርቦ። የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ ፥ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው። | [3] And when the tempter came to him, he said, If thou be the Son of God, command that these stones be made bread. |
| 4 እርሱም መልሶ። ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው። | [4] But he answered and said, It is written, Man shall not live by bread alone, but by every word that proceedeth out of the mouth of God. |
| 5 ከዚህ በኋላ ዲያቢሎስ ወደ ቅድስት ከተማ ወሰደውና እርሱን በመቅደስ ጫፍ ላይ አቁሞ። | [5] Then the devil taketh him up into the holy city, and setteth him on a pinnacle of the temple, |
| 6 መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል ተብሎ ተጽፎአልና የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ፥ ወደ ታች ራስህን ወርውር አለው። | [6] And saith unto him, If thou be the Son of God, cast thyself down: for it is written, He shall give his angels charge concerning thee: and in their hands they shall bear thee up, lest at any time thou dash thy foot against a stone. |
| 7 ኢየሱስም። ጌታን አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ደግሞ ተጽፎአል አለው። | [7] Jesus said unto him, It is written again, Thou shalt not tempt the Lord thy God. |
| 8 ደግሞ ዲያቢሎስ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው ፥ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ። | [8] Again, the devil taketh him up into an exceeding high mountain, and sheweth him all the kingdoms of the world, and the glory of them; |
| 9 ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው። | [9] And saith unto him, All these things will I give thee, if thou wilt fall down and worship me. |
| 10 ያን ጊዜ ኢየሱስ። ሂድ ፥ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው። | [10] Then saith Jesus unto him, Get thee hence, Satan: for it is written, Thou shalt worship the Lord thy God, and him only shalt thou serve. |
| 11 ያን ጊዜ ዲያቢሎስ ተወው ፥ እነሆም ፥ መላእክት ቀርበው ያገለግሉት ነበር። | [11] Then the devil leaveth him, and, behold, angels came and ministered unto him. |